በዚህ ለየት ባለ ጊዜ ተማሪዎች ትምህርታቸውን መማር እንዲቀጥሉ ለመደገፍ FCPS በኦገስት ወር ይህንን  የቅድመ ህጻንነት ልዩ ትምህርት የትምህርት ጥቅሎች/እሽጎች እንዲጠቀሙ ለማገዝ እያቀረበ ነው። በጥቅሉ ውስጥ ያሉት ተግባራት የተማሪዎችን ተሳትፎ ፣ ወሳኝ አስተሳሰብ እና የእንቅስቃሴ የመሳተፍ ፍላጎቶቻቸውን የሚደግፉ ክህሎቶችን እንዲለማመዱ እድል ይሰጣቸዋል። የቀረቡት ተግባራት በቤትዎ እና በማህበረሰብዎ ውስጥ በቀላሉ እንዲተገበሩ የተቀየሱ ናቸው። የ2020-21 የትምህርት ዓመትን ስንጀምር ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ለርቀት ትምህርት ለማዘጋጀት አንዳንድ ተወዳጅ አዳዲስ የበጋ እንቅስቃሴዎችን ይመለከታሉ፡፡ መደጋገም ለመማር እና ለችሎታ ማስተማር አስፈላጊ ነው ስለሆነም አብራችሁ ለመማር ይደሰቱ!

ጥቅሉ/እሽጉ እንዲሁ በBlackboard 24-7 ላይ ይለጠፋል።

“ጨዋታ የልጆች ሥራ ነው።” - Irene Sege

የልጅዎን ትምህርት በተሻለ ለመደገፍ በየቀኑ ከልጅዎ ጋር ለመጫወት ጊዜ ይመድቡ። ከልጅዎ ጋር የሚያደርጓቸውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ማዳበሩ ወጥነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል እንዲሁም ትምህርታቸውን ይደግፋል።  ደግሞም ተገቢ ከሆነ የፊት ጭምብሎችን መልበስ ለመለማመድ በጣም ጥሩ ጊዜ ነው።